# አድቫንስድ የትምህርት መርሃግብር (AAP) የአንደኛ ደረጃ ተከታታይነት ያላቸው አገልግሎቶች

ፌርፋክስ ካውንቲ የህዝብ ትምህርት ቤቶች (FCPS) የአድቫንስድ ተማሪዎችን ፍላጎት ለማሟላት በተሰጥዖ ልማት ጥረቶች እና በልዩ ልዩ የማስተማር ዘዴዎች ሁሉን ተማሪዎች አቅማቸውን አሟጠው እንዲጠቀሙ ለማትጋት ቁርጠኛ ነው።

FCPS ከK-12ኛ ክፍል ላሉ ተማሪዎች ተከታታይ አድቫንስድ የትምህርት አገልግሎቶችን ይሰጣል። የአገልግሎቶች ተከታታይነት አካሄድ ልዩ የተማሪ ፍላጎቶችን የሚገነዘብ እና አገልግሎቶችን በማጣመር ላይ የሚያተኩር እንጂ ለተማሪዎች በዘፈቀደ የሚመድብ አይደለም። ተከታታይነት ባለው አሰራር፣ ተማሪዎች እነዚህ ይኖሯቸዋል፡

- እመርታ እያሳዩ እያለ በተለዩ ዘርፎች ለጥልቅ የመማሪያ እድሎች በርካታ የማቅረቢያ ዘዴዎች።
- ተመሳሳይ የትምህርት ፍላጎት ያላቸው ተማሪዎች በክላስተር ቡድን በትምህርታቸው መበልፀጋቸውን እንዲቀጥሉ ።

መምህራን፣ የአድቫንስድ አካዳሚክ ሪሶርስ መምህራን (AARTs) እና የትምህርት ቤት አስተዳዳሪዎች በአንደኛ ደረጃ የሚከተሉትን የአገልግሎት ደረጃዎች ለማቅረብ አብረው ይሰራሉ።

## የጠለቀ ትምህርት አቅርቦት፣ ከK-6 ክፍሎች (ደረጃ I)

ሁሉም ተማሪዎች በጥልቀት የማሰብ፣ የማመዛዘን እና ችግርን ለመፍታት እድሎች አሏቸው።

- ሁሉም አስተማሪዎች በማስተማራቸው ጥልቅ የሆኑ እና የፈጠራ አስተሳሰብ ስልቶችን ይጠቀማሉ።
- የክፍል አስተማሪዎች ቢያንስ በሩብ አመት አንድ ጊዜ ከAAP ሥርዓተ ትምህርት ማዕቀፍ ቁሳቁሶችን በመጠቀም እድሎችን ይሰጣሉ።

የጠለቀ ትምህርት አቅርቦት ለሁሉም የFCPS ተማሪዎች ስለሆነ፣ የማጣራት ሂደት የለም።

## በተወሰኑ የትምህርት አይነቶች ላይ ያተኮረ አድቫንስድ መለያ ከK-6 (ደረጃ II)

አንዳንድ ተማሪዎች በተወሰነ የትምህርት ዘርፍ ጠንካራ ናቸው። የክፍል አስተማሪዎች በእዚህ/እነዚህ ዘርፍ/ፎች ላሉ ተማሪዎች የሚሰጠውን ትምህርት ማስተካከል ሊያደርጉ ይችላሉ።

- በእነዚያ የትምህርት አይነቶች ላይ የተለያዩ የቤት ስራዎችን እና መገልገያ ሀብቶችን መስጠት፣
- ተማሪዎችን በጥንካሬያቸው፣ በፍላጎታቸው እና በዝግጁነታቸው መቦደን እና፣
- ከAAP ሥርዓተ ትምህርት ማዕቀፍ ቁሳቁሶችን በመጠቀም ተጨማሪ ፈታኝ ስራዎችን ማቅረብ።

በተወሰኑ የትምህርት አይነቶች መለያ የተማሪ ፍላጎቶች በየዓመቱ በአካባቢ ትምህርት ቤት እንደገና ይገመገማሉ።

## የከፊል ጊዜ አገልግሎቶች ከ3-6 ክፍሎች (ደረጃ III)

አንዳንድ ተማሪዎች ከተወሰኑ የትምህርት ዓይነቶች መለያ በተጨማሪ በተለያዩ የትምህርት ዓይነቶች የአድቫንስድ የትምህርት ፍላጎቶች አሏቸው። የከፊል ጊዜ AAP አገልግሎቶች ያስፈልጋቸዋል።

- ተማሪዎች ተመሳሳይ የትምህርት ፍላጎት ካላቸው ሌሎች ተማሪዎች ጋር በየሳምንቱ በተለዩ ክፍሎች ወይም ሳምንታዊ በጋራ የሚሰጡ ትምህርቶች ከAART እና ከክፍል መምህር ጋር አብረው ይሰራሉ።
- አስተማሪዎች ከኤኤፒ ሥርዓተ ትምህርት ማዕቀፍ በቋንቋ ጥበባት፣ ሳይንስ፣ ማህበራዊ ጥናቶች እና/ወይም ሂሳብ የመርጃ መሳሪያዎችን የመጠቀም ተደጋጋሚ እድሎችን ይሰጣሉ።

የከፊል ጊዜ አገልግሎቶች እስከ 6ኛ ክፍል ድረስ ይቀጥላሉ። ተማሪዎች በየአመቱ ምዘና መውሰድ አያስፈልጋቸውም።

## የሙሉ ጊዜ አገልግሎቶች፣ ከ3-8 ክፍሎች (ደረጃ IV)

አንዳንድ አድቫንስድ ተማሪዎች በአራቱም አንኳር የይዘት ዘርፎች (ቋንቋ አርትስ፣ ሂሳብ፣ ማህበራዊ ጥናቶች እና ሳይንስ) ልዩ ትምህርት ያለው የሙሉ ጊዜ አድቫንስድ የትምህርት ፕሮግራም ያስፈልጋቸዋል።

ለሙሉ ጊዜ AAP አገልግሎቶች ብቁ የሆኑ ተማሪዎች በሙሉ ጊዜ ተሰባስበው እነዚህን ይወስዳሉ፡

- ከAAP ሥርዓተ ትምህርት ማዕቀፍ በቋንቋ ጥበባት፣ ሒሳብ፣ ሳይንስ እና ማህበራዊ ጥናቶች የሙሉ ጊዜ ቁሳቁሶችን መጠቀም፣ እና
- በፍጥነት፣ በጥልቀት እና በይዘት ውስብስብነት የሚለይ ስርዓተ ትምህርት።

የሙሉ ጊዜ አገልግሎቶች እስከ 8ኛ ክፍል ድረስ ይቀጥላሉ። ተማሪዎች በየአመቱ ምዘና መውሰድ አያስፈልጋቸውም።

## ለአድቫንስድ የትምህርት መርሃግብር አገልግሎቶች ማጣሪያ

ለሁሉም የFCPS የላቀ የአካዳሚክ አገልግሎቶች ብቁነትን ለመወሰን በርካታ የመረጃ ነጥቦች በጠቅላላ ይገመገማሉ። ኮሚቴዎች የተማሪዎችን ስራ ከAAP ትምህርቶች እድሎች፣ የተማሪ የማመዛዘን ምሳሌዎችን ወይም ከክፍል ውይይቶች እና ተግባራት የተሰጡ ተሰጥኦ ባህሪዎችን፣ የመሻሻል ሪፖርቶችን፣ የስኬት እና የችሎታ ውጤቶችን እና የወላጅ ግብአትን ይመለከታሉ። ኮሚቴዎች ተማሪዎች በክፍል ውስጥ የአካዳሚክ ውይይቶችን እና እድገትን ለመደገፍ ተመሳሳይ የአካዳሚክ ፍላጎቶች ያላቸውን የተማሪዎች ቡድን ማግኘት አለማግኘታቸውን ይመረምራል። በሁለገብ የማጣራት ሂደት ውስጥ ምንም አይነት የመረጃ ክፍሎች ግምት ውስጥ አልገቡም።

ለተወሰኑ የትምህርት አይነቶች አድቫንስድ መለያ እና የከፊል ጊዜ አገልግሎቶች የብቁነት ውሳኔዎች የሚወሰኑት በአካባቢው ትምህርት ቤት ኮሚቴ ነው፣ እንዲሁም የማጣራት ስራው በትምህርት ዓመቱ በሙሉ ይቀጥላል። ለተወሰኑ የትምህርት አይነቶች አድቫንስድ መለያ እና የከፊል ጊዜ አገልግሎቶች ለመጠቆም፣ የAAP በትምህርት ቤት የሚገኝ መጠቆሚያ/ሪፈራል ቅፁን በአካባቢው ትምህርት ቤት ለAART ያቅርቡ።

ለሙሉ ጊዜ አገልግሎት ብቁነት ውሳኔዎች የሚወሰኑት በካውንቲ አቀፉ ማዕከላዊ መራጮ ኮሚቴ ነው።

የሙሉ ጊዜ አገልግሎቶች ማጣራት የሚከናወነው በተወሰኑ የማጣሪያ ዑደቶች ውስጥ ነው፡-

- ከጥር ጀምሮ ለFCPS አዲስ ለሆኑ ተማሪዎች የበልግ/ፎል ማጣሪያ ይኖራል።
  - የበልግ/ፎል ማጣሪያ ጥቆማ/ሪፈራል የጊዜ ገደብ ከመጀመሪያው የትምህርት ቀን እስከ ጥቅምት 15 ነው።
- በFCPS ከ2-7ኛ ክፍል ለተመዘገበ/ች ተማሪ የፀደይ/ስፕሪንግ ማጣሪያ ይኖራል።
  - የፀደይ ማጣሪያ ጥቆማ/ሪፈራል የጊዜ ገደብ ከመጀመሪያው የትምህርት ቀን እስከ ታኅሣሥ 15 ነው።

ከ2-7ኛ ክፍል ላሉ ተማሪዎ ጥቆማ/ሪፈራል ከማቅረብዎ በፊት እባክዎ የፈተና ውጤቶችን አይጠብቁ። ከላይ ከተጠቀሱት የሙሉ ጊዜ አገልግሎቶች ጥቆማ/ሪፈራል የጊዜ ገደቦች በኋላ የሚቀርቡ ጥቆማዎች ተቀባይነት የላቸውም።

ለሁሉም አድቫንስድ የትምህርት መርሃግብሮች የጥቆማ/ሪፈራል ቅፆች እዚህ ይገኛሉ https://www.fcps.edu/node/38893.

ለተጨማሪ መረጃ፣ እባክዎ የAAP ድረገፅን እዚህ ይጎብኙ: https://www.fcps.edu/registration/advanced-academics-identification-and-placement/current-fcps-students.

## የችሎታ ፈተና

FCPS የችሎታ ፈተናን ለአድቫንስድ የአካዳሚክ አገልግሎቶች አጠቃላይ የማጣሪያ ሂደት እንደ አንድ ግብዓት ይጠቀማል። የፈተና ውጤቶች ሁሉን አቀፍ የማጣሪያ ሂደት ውስጥ እንደ አንድ አካል አይቆጠሩ ወይም ቅድሚያ አይሰጣቸውም።

- ሁሉም የ1ኛ ክፍል ተማሪዎች የናግሊየሪ ቃላዊ ያልሆነ የችሎታ ፈተና (NNAT) ይወስዳሉ።
- ሁሉም የ2ኛ ክፍል ተማሪዎች የግንዛቤ ችሎታ ፈተና (CogAT) ይወስዳሉ።
- NNAT እና/ወይም CogAT ከ3-6ኛ ክፍል ላሉ ተማሪዎች በመደበኛ መርሐግብር በተያዘላቸው የፈተና ቀነ ገደቦች ውስጥ የችሎታ ፈተና ውጤት ለሌላቸው ተማሪዎች ሊሰጥ ይችላል።

ከ3-6ኛ ክፍል፣ ወላጆች ወይም አሳዳጊዎች  ለCogAT ወይም NNAT የአንድ ጊዜ እንደገና መፈተንን ሊጠይቁ ይችላሉ። ጥያቄዎች በበልግ/ፎል የፈተና ቀነ ገደቦች ወቅት  መቅረብ አለባቸው። እባክዎ የትምህርት ቤቱን የፈተና አስተባባሪ Melissa Beland (mgbeland@fcps.edu) *(name and contact information)* እስከ መስከረም 15 ድረስ ለCogAT ወይም ጥቅምት 15 ለNNAT ያግኙ።

## የአንደኛ ደረጃ የወላጅ መረጃ ስብሰባ

የወላጅ መረጃ ስብሰባ የሚካሄድው በ Marshall Road ES *(school name)* በ Thursday, October 19 *(date)* በ 6:30 pm *(time)*። AART ስለ የአገልግሎት ደረጃዎች መረጃ ይሰጣል፣ የማጣሪያ ሂደቶችን ያብራራል፣ እና ስለአድቫንስድ የትምህርት አገልግሎቶች ጥያቄዎችን ይመልሳል።

## ወጣት ተማሪዎች

የFCPS ወጣት ምሁራን ሞዴል ከልጅነታቸው ጀምሮ ከፍተኛ የአካዳሚክ አቅም ያላቸውን ተማሪዎች በአድቫንስድ የአካዳሚክ መርሃ ግብሮች በታሪክ ዝቅተኛ ውክልና ካላቸው ቡድኖች ለመለየት እና ለማረጋገጥ ይሰራል። የሞዴሉ ግብ ለወጣት ምሁራን በአንደኛ ደረጃ፣

መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ እና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የአድቫንስድ የአካዳሚክ እድሎች የማግኘት እና ስኬት መሰናክሎችን ማስወገድ ነው።

### ሁለት-እጥፍ የተለዩ/Twice-Exceptional (2e)

አድቫንስድ የመማር ፍላጎት ያላቸው አንዳንድ ስጦታ ያላቸው ተማሪዎች የመማር እክል/ዲስአቢሊቲ ሊኖራቸው ይችላል። ሁለት እጥፍ የተለዩ (ወይም "2e") ተማሪዎች የአድቫንስድ መርሃግብር በሚያገኙበት ጊዜ በጥንካሬዎች ላይ የተመሰረተ ትምህርት ያስፈልጋቸዋል። የFCPS ተከታታይ የAAP አገልግሎቶች የተማሪ ፍላጎቶችን ለማሟላት በርካታ አማራጭ መንገዶችን ይሰጣል እንዲሁም የመማር ፈተናዎቻቸውን ይደግፋል። ትምህርት ቤቶች እና ቤተሰቦች የ2e ተማሪዎችን እንዴት መለየት እና ማገልገል እንደሚችሉ እንዲረዱ FCPS የ2e መመሪያ መጽሃፍ አዘጋጅቷል። እነዚህን የመገልገያ ሀብቶች www.fcps.edu በመሄድ እና "2e."ን በመፈለግ ማግኘት ይችላሉ።

## በመለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ወይም ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አድቫንስድ የትምህርት መርሃግብሮች

### የመለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት AAP

በመለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ደረጃ የአድቫንስድ ኮርስ ስራ ምዝገባ ክፍት ነው። ሁሉም ተማሪዎች በየትምህርት አመቱ ቢያንስ ለአንድ አበይት/ኦነርስ ትምህርት በጥንካሬያቸው እና/ወይም በፍላጎታቸው መስክ እንዲመዘገቡ ይበረታታሉ።

ለሙሉ ጊዜ አገልግሎት ብቁ የሆኑ ተማሪዎች በአድራሻቸው የተመደበውን የመለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ማዕከል ለመከታተል ወይም በራቻቸው ትምህርት ቤት በአራቱ ዋና ዋና የይዘት ዘርፎች በአበይት/ኦነርስ የትምህርት አይነቶች የመመዝገብ አማራጭ አላቸው።

### የሁለተኛ ደረጃ AAP

በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ደረጃ የአድቫንስድ ኮርስ ስራ ምዝገባ ክፍት ነው። ሁሉም ተማሪዎች ከ9ኛ ክፍል ጀምሮ ቢያንስ አንድ አበይት/ኦነርስ ኮርስ እንዲመዘገቡ ይበረታታሉ። በFCPS ውስጥ ያለ እያንዳንዱ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በመርሃግብሩ እና በትምህርት ቤቱ በመንተራስ፤ 10 እና 11ኛ ክፍል የሚጀምሩ የAP፣ IB ወይም ሁለትዮሽ/Dual የምዝገባ የትምህርት አይነቶችን ይሰጣል፣ ።

ስለ መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ወይም ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አገልግሎቶች ተጨማሪ መረጃ በአድቫንስድ አካዳሚክ ፕሮግራምስ ድረ ገፅ ሊገኝ ይችላል: https://www.fcps.edu/academics/academic-overview/advanced-academic-programs.